# ይድረስ ለአዲስ ጉዳይ መፅሔት

## የሃሳብ ፍጭትን በመሸሽ ዜጎችን መፈረጅ ያሳፍራል

መሐሪ ይፍጠር

yiftermehari@gmail.com

(ክፍል አንድ)

አዲስ ጉዳይ መፅሔት በሚያዝያ 05 ቀን 2005 ዓ.ም ዕትሙ ላይ ‘ዐብይ ጉዳይ’ በተሰኘው ባለቤት አልቦና ከሙያው አኳያ የጋዜጣው አቋም ተደርጎ በሚወሰደው አምዱ ስር “መንግስት ሆይ፣ ሺህ ዓመት ንገስ” በሚል እንዲሁም ይህንኑ አምድ በመደገፍ ትክክለኛ አቋሙ በሆነው ርዕሰ አንቀፁ ላይ “አወዳሹን አድልቦ ነቃሹን ማመንመን” በተሰኘ ርዕስ ለፃፈው በጥናት ላይ ያልተመሰረቱ፣ ጥላቻን ያዘሉ፣ የጋዜጠኝነት ስነ-ምግባርን ያልጠበቁ፣ መረን የለቀቁና ፅንፈኛ ዲያስፖራዎች በየሚዲያዎቻቸው ከሚያራግቡት አጀንዳ ጋር ተመሳሳይ በሆኑት ዘገባዎች ላይ የማምንበትን ሃሳብ በመግለፅ ለአይጋ ፎረም ድረ-ገፅ፣ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣና ለመፅሔቱ ዝግጅት ክፍል እንደ ዜጋ በየአድራሻው ልኬላቸዋለሁ።

ይሁንና አይጋ ፎረም ድረ-ገፅ እና አዲስ ዘመን ጋዜጣ በሚያዝያ 17 እና 18 ቀን 2005 ዓ.ም በሁለት ተከታታይ ዕትሞቹ ሃሳቤን ለንባብ ሲያበቁት /በዚህ አጋጣሚ የዝግጅት ክፍሎቹን የዜጎችን ሃሳብ ሃላፊነት ወስደው በማንሸራሸር ረገድ ላሳዩኝ አክብሮት ሳላመሰግናቸው አላልፍም/፤ ስለ “ነፃ” ፕሬስ እሟገታለሁ የሚለው አዲስ ጉዳይ መፅሔት ግን በአድራሻው (addisguday@yahoo.com) ብልክለትም ምናልባትም ራሱን ተችቼ በመፃፌ ሳቢያ አሊያም በኢዲቶሪያል ፖሊሲው ውስጥ /ካለው ማለቴ ነው/ ‘ወገንተኝነታቸው ለመንግስት የሚመስሉ ፅሑፎችን አናስተናግድም’ የሚል አሰራር ኖሮት ነው መሰል ሃሳቤን አፍኖታል ወይም በጋዜጠኝነት ቋንቋ ፅሑፌን ‘ቅርጫት ውስጥ ከትቶታል’። መፅሔቱ ያደረገው ነገር ቢኖር በሚያዝያ 26 ቀን 2005 ዕትሙ ‘ሐሳብ አለኝ’ በተባለ አምዱ ስር ‘ተስፋዬ መኮንን’ በተባሉ ምናባዊ ሃያሲው አማካኝነት “ትችት ያበረታታል፣ ስድብ ግን ያስተዛዝባል” በሚል ርዕስ /የትኛው ስድብ እንደሆነ ባላውቀውም/ አዲስ ዘመን ላይ የወጡትን ተከታታይ ፅሑፎች በመጥቀስ ፅሑፌን ሳይሆን እኔን በመተቸት መፈረጅ ነው—መስመር በመስመር በመሄድ ለአቶ መሐሪ ፅሑፍ ምላሽ በመስጠት ጊዜያችንን አናባክንም በማለት።

እናም መፅሔቱ ጥሩ መስሎ የታየው መንገድ እኔን በመፈረጅ ‘የመንግስት ወኪል ነው፣ ማንነቱን እናውቀዋለን…ምንትስ’ በማለት ያልተገባ ታፔላን ላዬ ላይ መለጠፍ ነው። ይህ ደግሞ የሃሳብ ፍጭትን በመሸሽ ዜጎች ህገ-መንግስቱ የሰጣቸውን መብት በመጠቀም የሚያምኑበትን አቋም እንዳያራምዱ ያለ አንዳች ተጨባጭ አመክንዩ መፈረጅ በመሆኑ አሳፋሪ ነው፤ አስነዋሪም ሆኖብኛል። በተለይም ሃሳቡ ለይስሙላም ቢሆን አንድ ራሱን “የነፃው ፕሬስ አካል ነኝ” እያለ ከሚጠራ የሚዲያ ተቋም የተሰነዘረ በመሆኑ ፍረጃውን ይበልጥ ነውረኝነት ያላብሰዋል። እርግጥ ማንም ሰው የፈለገውንና የሚያምንበትን ጉዳይ ቢፅፍ መብቱ መሆኑን መፅሔቱ ያጣዋል ብዬ አልገምትም። የግድ እኛን ካልመሰልክ ሊባልም አይገባውም። እንዲህ ዓይነቱ እሳቤ የራስን እምነት በሌሎች ላይ በኃይል መጫንና ጭልጥ ያለ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ዕይታ በመሆኑ አመለካከቱን በፀጋ ‘አሜን’ ብዬ ልቀበለው እንደማልችል የዝግጅት ክፍሉ ሊያውቀው ይገባል—የምንኖረው ዴሞክራሲያዊ ሀገር ውስጥ ነውና። ያም ሆነ ይህ ግን አሁንም ተስፋ ሳልቆርጥ መፅሔቱ ለሰጠኝ ምላሽ ይህን ፅሑፍ ለሶስቱም ዝግጅት ክፍሎች በምላሽነት ልኬዋለሁ— ፅሑፌንም ለንባብ እንደሚያበቁት በመተማማን።

እንደሚታወቀው አንድ የሚዲያ ውጤት ከሙያው ስነ-ምግባር አፈንግጦ ራሱ ያለአንዳች ገደብ ጥናትና ምንጭ አልባ ጉዳዮችን እያተመ ሲያሰራጭ ትክክል የሚሆንበት፤ ሌሎች ደግሞ የራሳቸውን እምነት በማቅረብ ሊሞግቱት ሲነሱ ትክክል የማይሆኑበትና የሚፈረጁበት አሰራር ሊኖር አይችልም። ምክንያቱም የሀገራችን ህገ-መንግስት ለአዲስ ጉዳይም ሆነ ለእኔ የሰጠው ሃሳብን የመግለፅ መብት እኩል በመሆኑ ነው። መፅሔቱ አንድ ተቋም ስለሆነ እኔ ደግሞ ዜጋ ስለሆንኩ የምነፈገው መብት ሊኖር አይችልም። የሁለታችንም መብት እኩል ነው፤ አይበላለጥም። እርግጥ ነው መፅሔቱ የእኔን ፅሑፍ ያለማውጣት መብት እንዳለው እገነዘባለሁ። ምክንያቱም መመራት ያለበት የፋይናንስ ምንጩን ሊደጉመው ከሚችለው ፖለቲካል-ኢኮኖሚ አስተሳሰብ እንጂ ሀገር በቀል እሳቤዎችን ማራመድ ስለማይጠበቅበት ነው። እናም መብትና ግዴታዬን የማውቅ ዜጋ እንደመሆኔ መጠን፤ መፅሔቱ ፅሑፌን ባለማተሙ አልደነቅም—ምንም እንኳን እንደ አንድ የሚዲያ ውጤት የዜጎችን ሃሳብ ያለገደብ የማንሸራሸር ማህበራዊ ኃላፊነቱን ባይወጣም።

ያም ሆነ ይህ ግን “ምን ዓይነት ፕሬስ ይበጀናል?” ለሚለው ፅሑፌ መፅሔቱ እጅና እግር አበጅቶለትና ያላልኩትን ሁሉ አጭቆበት ወደ ሰጠው ምላሽ በቅድሚያ ከማምራቴ በፊት አንድ ጉዳይን ማንሳት እሻለሁ። እርሱም በአፃፃፍ ዘዴያቸው ከ‘ዐብይ ጉዳይ’ አምድ ፀሐፊው ጋር አንድ ዓይነት የሆኑብኝና ለፅሑፌ ምላሽ ሰጥተዋል የተባሉት ‘አቶ ተስፋዬ መኮንን’ የተለዩ አንባቢ ናቸው ብዬ ለማመን የምቸገር መሆኔን ነው። ለምን ቢባል፤ ያለ አንዳች ጥናትና በዘፈቀዳዊ ጥላቻ የመንግስት ሚዲያዎችን ‘የሚሰማቸው የለም፣ አቅማቸው የተመናመነ ነው…ወዘተርፈ’ በማለት የማጥላላት ዘመቻ የከፈቱት እንዲሁም የግል ፕሬሱን ከባድና አሳፋሪ ህፀፅ ሳያዩ ሚዛናዊ ባልሆነና

እርስ በእርሱ በሚጋጭ አተያይ መልሰው መንግስት “ነፃ” ፕሬሱን እያቀጨጨ የራሱን ሚዲያ ያደልባል በማለት ለመወረፍ የሞከሩት ስውሩ ፀሐፊ፤ እኚሁ መልስ ሰጡ የተባሉት ግለሰብ መሆናቸውን ከፅሑፋቸው በመገንዘቤ ነው። በእኔ እምነት መፅሔቱ ያደረገው ነገር፤ በጉዳዩ ላይ የፃፉትንና ከጋዜጠኝነት ስነ-ምግባር ውጪ በየትኛውም የጋዜጠኝነት ስማቸውን እንዲገለፅ የማይፈለጉት የፈሪ ድንጋይ ወርዋሪው አዘጋጅ መልስ እንዲሰጡ ከተደረገ በኋላ፤ ከፅሑፋቸው ስር ‘ከአዘጋጁ’ ተብሎ እጅና እግር የሌለውን የሰውዬውን ዘገባ በመድገም ‘ቃለ-ህይወት ያሰማልን’ ብሎ ማምታትን ነው። እናም ራሱም የዝግጅት ክፍሉ ‘ከሰውዬው’ ሃሳብ ጋር እንድሚስማማና ሙሉ ለሙሉ ፅሑፋቸውን እንደሚጋራ እንዳልካደው እንዲሁም አዘጋጁ ግለሰቡን ‘ፀሐፊያችን’ እያሉ በመጥራታቸው፤ የዘገባው ባለቤት ዝግጅት ክፍሉ መሆኑን ለመጠራጠር አልፈልግም።

እስቲ ለማንኛውም ‘በአቶ ተስፋዬ መኮንን’ ስም ስለተዘጋጀውና ዕውቀት ከታከለበት ምላሽ ይልቅ ጨዋነት በጎደለው ሁኔታ የፀሐፊውን ስብዕና በማንቋሸሽ ላይ ስለተመሰረተው ፅሑፍ ጥቂት ልበል። እርግጥ አንድ ፀሐፊ ለአንድ ጉዳይ ምላሽ ለመስጠት በነገሩ ላይ በቂ ጥናት በማድረግ ማለፊያ ዕውቀት ሊኖረው ይገባል። በተለይም ምላሹ በመፅሔት ላይ የሚሰጥ ከሆነ፤ ከሙያ አንፃር መፅሔት ያለው ቦታ ከጋዜጣ የተሻለ በመሆኑ በጥልቅ ጥናት ላይ የተመረኮዘና አሳማኝ መሆን ይኖርበታል። ይህም ጋዜጠኛው የተሟላ ዕውቀት እንዲኖረው ያደርገዋል። በእኛ ሀገር ግን እንደ አዲስ ጉዳይ ዓይነቶቹ አንዳንድ መፅሔቶች እንዲህ ዓይነቱን አካሄድ ለመከተል አይፈልጉም። ከዚህ ይልቅ አንድም ስሜት የሚኮረኩሩ /sensetional/ እና የአሚሙቅ ጋዜጠኝነት ዘዴን /yellow journalism style/ ይከተላሉ፣ አሊያም በጥናት ላይ ባልተመሰረተና በዕውቀት አጠርነት መንግስትን ለማብጠልጠል “ይባላል፣ ይነገራል፣ ይወራል…ወዘተ.” የሚሉ ኢ-ሙያዊ አሉባልታዎችን እንደ መደበኛ አሰራር ይከተላሉ— እዚህ ላይ የአዲስ ጉዳዩን ‘ዐብይ ጉዳይ’ አምድ ተከታታይ “የፕሬስ ነፃነት” መዝሙሮችንና ሌሎች በዕውቀትና በጥናት ላይ ያልመሰረቱ ዘገባዎችን ያስታውሷል! በእኔ እምነት እነዚህ የሚዲያ ውጤቶች ይህን ሙያዊ ቀኖና ለመከወን የማይፈልጉት በጉዳዩ ላይ የሚሉት ነገር ስለሌላቸው ብሎም ከህትመት ከሚያገኙት ገቢ አላስፈላጊ ጥቅም ማጋበስ ስለሚሹ ነው። ይህም ተግባራቸውም ራሳቸውን በዕውቀት አብቅተው ህዝብን በሚዲያ ከማገልገል ይልቅ፤ ቅንጭብጫቢና ጥራዝ ነጠቅ አባባሎችን በመጠቀም የህዝብ አገልጋይ ሳይሆኑ ራሳቸው በፕሬሱ እየተገለገሉ መሆናቸውን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው። በመሆኑም አዲስ ጉዳይ መፅሔት ለፅሑፌ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ወደ ወረደው ግለሰባዊ ትንተና መግባት የፈለገው ከእነዚህ እጥረቶቹ ተነስቶ በመሆኑ አልተቀየምኩትም።

ያም ሆነ ይህ ግን የመፅሔቱን ምላሽ መመልከቱ የሚከፋ አይመስለኝም። መፅሔቱ “መንግስት ሆይ፣ ሺህ ዓመት ንገስ” የሚለው ፅሑፌ ‘ምናልባት መንግስት ይህንን ቢያነብና የተጠቆሙትን ማስተካከያዎች ቢጠቀምባቸው’ በሚል ነው ያዘጋጀሁት ባይ ነው።… እርግጥም

ሃሳቡ እንዲያ ከሆነ ማለፊያ ነበር። ግን ደግሞ አይደለም። መቼም እንዲህ ዓይነቱን “ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ” አባባልን ‘ይገርማል’ ከማለት ውጪ ምንም ልለው አልፈልግም።...በመጀመሪያ ደረጃ መፅሔቱ በፅሑፉ ላይ ያሰፈራቸው ጉዳዩች የመንግስት ሚዲያንና መንግስትን ያለ ምንም አስረጅ የሚያጣጥሉ እንጂ ፀሐፊው የበግ ለምድ ለብሰው ‘መንግስት እንዲያሰተካክለው ብዬ ነው’ እንዳሉት አይደለም። እርግጥም ፅሑፉ የመንግስት ሚዲያዎችን “የአዝማሪ ስራን የሚያከናውኑ” እያሉ ለህዝብ የሚፈፅሙትን ተግባራት ጥላሸት ለመቀባት፣ ያለ ምንም ተጨባጭ ማስረጃ “እምነት የማይጣልባቸው፣ አንባቢ፣ ተመልካችና አድማጭ የሌላቸው፣ በመኖርና ባለመኖር መካከል የሚንገታገቱ...ወዘተ.” እያሉ አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ ለማንቋሸሽ ያለመ ነው። ከዚህ ባሻገርም መንግስት ለፕሬሱ መዳበርና መጎልበት ምንም ተግባር እንዳላከናወነ በጭፍን ጥላቻና አመክንዮ በጎደለው መንገድ በደፈናው “በኢትዮጵያ ያለውን ፕሬስ ለማሳደግ አንዳች ሚና አልተጫወተም፣ ከዚህ ይልቅ የሚተጋው ጀፈርሰን እንደሚጠላው ዓይነት ጋዜጣ የሌለበት መንግስት ለመመስረት ነው” የሚሉ ከዕውነታው ያፈነገጡና ተዓማኒነት የጎደላቸውን የስም ማጥፋት ዘመቻ ማካሄድ ነው። እንግዲህ ዓይነቱን አስገራሚ፣ ቅንነት የጎደለውና መንግስትንና ሚዲያውን የማጣጣል ዘመቻን ነው—መፅሔቱ ‘መንግስት ቢያስተካክለው ብዬ ነው’ በማለት በካፈርኩ አይመልሰኝ ሊሞግተኝ የሚከጅለው።

መፅሔቱ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትንና የ“ነፃ” ፕሬስ ልዩነቶችን ለራሱ የፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ሲል እኔ ያላልኩትንም ሆን ብሎ ለማጣረስ ሞክሯል። እኔ በፅሑፌ ላይ ያሰፈርኩት ፕሬስ እንደማንኛውም ተቋም ፍፁማዊ ነፃነት /absolute freedom/ ስለሌለው “ነፃ” የሚባል ሚዲያ የለም በሚል ያቀረብኩትን ሙግት፤ ፀሐፊው ግን ወትሮም አካሄዳቸው ጤነኛ ስላልሆነ አሊያም የሚመልሱት መልስ ስለሌላቸው የሰው ልጅ የማይገሰስ መብት ከሆነው ሃሳብን በነፃነት ከመግለፅ መብት ጋር የግድ አጣብቀው ሊሰፉት ሞክረዋል። እንዲሁም ለፅሑፌ ማጣቀሻ ያደረኳትንና የበርካታ ዓመታት የጋዜጠኝነት ስራ ልምድ ባለቤት የሆነችውን ዕውቋን የኒው ታይምስ ጋዜጣ ኤዲተር ታቲያና ሪፕኮቫን መቼም ልማድ አይተውምና በነካ አጠልሺ እጃቸው ሊያጣጥሏት እንዲሁም ስለ ጋዜጠኝነት ህግ የተናገረችውን አጣሞ ተርጉሚል በሚል የጥንቆላ እሳቤ የፅሑፌን ፈር ለማሳት ሞክረዋል። ይሁንና እኔ የጠቀስኩት ሪፕኮቫ “Newspapers in an Emerging Democracy” በሚል መፅሐፏ “Is there an independent/free press?” በሚል ንዑስ ርዕስ ስር “Press ‘independence/freedom’ in this complex world cannot be absolute. How can an independence/free press be “free” of government laws like libel law, like labour law, like owner economic control and a journalist personal bias?... therefore, the word ‘independent/free’ is not fully self-defining.” /በዚህ ውስብስብ ዓለም ውስጥ የፕሬስ “ነፃነት” ፍፁማዊ ሊሆን አይችልም። አንድ ፕሬስ እንዴት ነው ከስም ማጥፋትና ከስራ የመንግስት ህጎች

እንዲሁም ከባለቤቱ የኢኮኖሚ ቁጥጥርና ከጋዜጠኛው ሚዛናዊ አለመሆን “ነፃ” ሊሆን የሚችለው?...በመሆኑም “ነፃ” የሚለው ቃል ራሱን ችሎ የሚቆም አይደለም/ በማለት ያሰፈረችውን ሃቅ በዘገባቸው ላይ መጠራጠር የሚያበዙት ፀሐፊው፤ አቶ መሐሪ አጣሞ ነው የተረጎመው በማለት ምንነቱን ስለማያውቁት መፅሐፍ በድፍረት ለመናገር ሞክረዋል–በአላዋቂ ሳሚነት።

ታዲያ እዚህ ላይ ያስገረመኝ ነገር እኔ የግለሰቧን መፅሐፍ በአግባቡ ጠቅሼ ሳበቃ፤ መፅሔቱ ደግሞ በሴረኝነት ንድፈ ሃሳብ ትንተናው /Conspiracy Theory Analysis/ ታግዞ “አንዲት ኤዲተር ስለ ጋዜጠኝነት ህግ ተናገረች የተባለውን ነገር አጣመው በመተርጎም...” እያለ ያነሳሁትን ጭብጥ ሳይሆን የእኔን የመተርጎም ብቃት ነብይ ሆኖ ለመተንበይ መከጀሉ ነው። ግና ዕውን ሪፖርኮቫ ያለችው የመፅሔቱ ስውር ፀሐፊ እንዳሉት ስለ ጋዜጠኝነት ህግ ነውን?– በፍፁም አይደለም። እርሷ ያለችው ስለ ፕሬስ “ነፃነት” ነው። ፕሬስ በመንግስት የህግ ማዕቀፎች፣ በባለቤቱ ርዕዮት-ዓለም ዝማሜ ምክንያት እንዲሁም ጋዜጠኛው ራሱ ሰው እንደመሆኑ መጠን በሚያምንበት ጉዳይ ሊሳብ ስለሚችል “ነፃ” ሊሆን አይችልም እያለችን ነው። ይህ ዕውነታም “ነፃ” የሚባል ሚዲያ የሌለ መሆኑን ነው የሚያመለክተው።...እናስ ስውሩ ፀሐፊ ሆይ!...ኤዲተሯ ‘ስለ ጋዜጠኝነት ህግ ነው የተናገረችው’ ያሉትን ቅጥፈት ከወዴት ነው ያመጡት?...ምናለበት ቢያንስ የማያውቁትን ነገር እንኳን በጭፍን ጥላቻ ከመፈረጅ ቢቆጠቡ?...ምናለበት ምንም ተጨባጭ ጉዳይ ሳይዙ ሐሰትን በመፃፍ ሰዎችን ለማደናገር ባይታትሩ?...ምናለበት ሚዲያውን የህዝብ ማገልገያ ሳይሆን የአሉባልታ ማሻሻጫና በህዝብ እየተገለገሉ ኪራይ መሰብሰቢያ ባደርጉት?..ስውሩ ፀሐፊ...እውነት እውነት እልዎታለሁ እንዲህ ዓይነቱ ውሸት ቀማሪነት ከአንድ የሚዲያ ባልደረባ ለዚያውም “ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ” እንዲሉ “የነፃው ፕሬስ አድናቂ ነኝ” እያለ ከሚመፃደቅ መፅሔት “ጋዜጠኛ” የሚጠበቅ አይመስለኝም። እጅግ ያሳፍራል፤ያስተዛዝባልም። ...ውድ አንባቢዎቼ በሌሎቹ የመፅሔቱ ምልከታዎች ላይ ያለኝን ምላሽ በክፍል ሁለት ዕሑፌ ላይ እመለስበታለሁ።